ማርች 15 1994

## ለማርች 28 አዲስ አበባ ስብሰባ እንዲደረግ በጂሚ ካርተር ስለቀረበው ሃሳብ

በዚህ ጥያቄ ላይ ባለፈው ሳምንት ከላኩት መልእክት ብዙም የተለየ ሃሳብ የለኝም::
አንዳንድ ለውይይት የሚረዱ ዝርዝር ነገሮች እንደሚከተለው አቀርባለሁ::
1ኛ/ ባለፈው ጊዜ ስላቀረብኩት ሃሳብ ምን እንደምታስቡ በውል ስለማላውቅ አሁን በዚ
ያው መንፈስ እቀጥላለሁ:: ግን ባለፈው ያነሳኋቸው ነጥቦች በተለይ አበራ የማነአብ
በቅንጅቱ መሪነት ተወንጅሎ በእስር እስካለ ድረስ ሌሎች የቅንጅት መሪዎች አዲስ አበ
ባ ሄደው መደራደራቸው፣ ግልጽ የሆነና ህዝቡም የሚያውቀው የአጀንዳ ነጥብ ሳይኖር ድ
ርድር መክፈቱ፣ የነገሮችን ቅደም ተከተል በትክክል አስቀምጦ ከዚህ ድርድር የምንፈል
ገውን ግብ ከወዲሁ ለይተን አለማወቅ...እነዚህ ሁሉ ሊያስከትሉ የሚችሉትን የፖለቲካ
ችግር በሚገባ ማጤን አስፈላጊ ይመስለናል::
2ኛ/ የቀደመውን ደብዳቤ ሳንመልስ ጂሚ ካርተር ደግሞ ሌላ ደብዳቤ ልከዋል::ከደብዳ
ቤው እንደሚታየው ሰውየው በዚህ ስብሰባ ሩቅ ለመሄድ ያቀዱ ነው የሚመስለው:: በእና
ቢ የቀረቡት ነጥቦች ምንም ችግር የላቸውም:: እንዲያውም የዚህ የመጀመሪያው ስብሰባ
ዋና ከሚባሉት አጀንዳዎች እኛን ተቃዋሚ ኃይሎችን ብቻ አመጽን አውግዙ ከማለት ዋናው
ዝሬ በሃገሪቱ ያለው የታጠቀ አመጽና ኃይልም ውይይቶች በሰላም ይፈቱ፣ አመጽን እንተ
ው ብሎ አብሮን የሚፈርምበት ሁኔታ ለመፍጠር መሆን አለበት:: ጂሚ ካርተር ያቀረቡት
የመወያያ ነጥብ ሃሳብ ላይ በሲ የተጠቀሰው ግማሹ ሲስማማኝ ግማሹ ደግሞ ጊዜው አይደ
ለም እላለሁ:: "የውይይቶቹ ተቀዳሚ ዓላማ እንዴት ሁሉም ወገኖች በመካሄድ ላይ ባለ
ው የፖለቲካ ሂደት በአንድ ላይ እንደሚሰሩ ለመወሰን ነው::" የሚለው ክፍል ደህና ነ
ው:: የተቃዋሚ ድርጅቶች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ህጋዊ ሰውነት የሚያገኙበትን ሁኔታ
ለመደራደር ያመቸናል:: ከዚያ በኋላ ያለው የምርጫ፣ ወዘተ ጥያቄ ግን እኛ አዲስ አ
በባ ከመገኘታችንና ከመመዝገባችን በፊት የምንወያይበት ባይሆን ጥሩ ነው:: በዲ ላይ
ያነሱትና መግለጫ አሰጥበታለሁ ያሉት ነጥብ ምንም ችግር የለውም:: ከነጻና ርእታዊ
ምርጫ አስተሳሰባችን ጋር የሚሄድ ነው:: ነገ ኢህአዴግ በጸረዲሞክራቲክ ምርጫው አገ
ፋበታለሁ ካለ እሳቸውንም እየጠቀሰን /ሃቀኛ ከሆኑ ደግሞ ከኛ ጉን ተሰልፈው/ እንቃ
ገልበታለን:: ስለዚህ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም::
3ኛ/የአበራ ጉዳይን በሚመለከት በኛ በኩል የሱን መፈታት የቅድሚያ ቅድሚያ የምንሰጠ
ው ጉዳይ ነው::እሱን ካልፈቱት እንሄድ ወይስ አንሄድ የሚለውን ጥያቄ አስበንበት ተ
ወያይተንበት መልሳችንን እንሰጣለን:: እስከዚያው ግን አሁን ለዚህ ለካርተር ደብዳቤ
መልስ ሲሰጥ እሳቸውን በሳቸው አማካኝነት ደግሞ እነመለስን መጠየቅ የሚቻለው እንደሚ
ከተለው ይመስለናል:: "አቶ አበራ የማነአብ የቅንጅቱ የውጭ ግንኙነት ሃላፊ ለአዲ
ስ አበባው የሰላምና እርቅ ጉባኤ ሄደው እንደታሰሩ እስካሁን አልተፈቱም:: የተወነጀ
ሉት በቅንጅቱ መሪነታቸውና ቅንጅቱ ፈጸመው በተባለው ወንጀል ነው::' በሌላ በኩል ደ
ግሞ ለውይይቱ የቅንጅቱ መሪዎች አዲስ አበባ መጥተው ከመለስ ተገናኝተው ያለአንዳች
ስጋት ሊመለሱ ይችላሉ፣ ዋስትና ይሰጣል ተብሏል:: ባለፈው በጻፍንልዎ ደብዳቤ በዚህ
ስብሰባ ላይ ከመንግሥትም ከተቃዋሚም ወገን ከፍተኛ መሪዎች መገኘታቸው እንደሚመረጥ
ጠቁመናል::በኛ በኩል ለምሳሌ ሊቀመንበራችንን ብንልክ የውጭ ጉዳይ ኃላፊያችን ታስሮ
ዋናው መሪያችን እንደማይታሰሩ ምን ዋስትና አለን? እሳቸው ገብተው የመውጣት ዋስትና
እስካገኙ ድረስ በድርጅቱ ወንጀል ተከሰሰ የተባለው ምክትላቸው በእስር የሚቆይበት ም
ን የፖለቲካ፣ የህግና የሞራል ምክንያት አለ?ይህ ጥያቄ አባሎቻችንንም ሆነ ብዙውን
ህዝብ ግራ ያጋባ ጥያቄ በመሆኑ በዚህ ላይ እርስዎም ሆኑ እነአቶ መለስ ያላቸውን አ

 

ስተሳሰብ በአስቸኳይ ብታስታውቁን ለስብሰባው ለምናደርገው ዝግጅት በጣም ይረዳናል" በሚል መልክ ሊጻፍላቸው ይቻላል:: ለጊዜው::

45/ሌላ እንግዲህ በዚህ የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ስለምን እንደምንወያይ ከሁላችንም በኩል ግልጽ ብንሆን ከወዲሁ ለስብሰባው መሳካት ብዙ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተጠቅሶላቸው ሁለት ጉዳዮችን ማስፈር ይቻላል:: እንደኛ በኛ በኩል ለዚህ ለመጀመሪያው ስብሰባ መቅረብ አለባቸው የምንላቸው ነጥቦች እነሱም፤

ሀ/ የአብራ መፈታት ጉዳይ ከፍ ብዩ ባስፈርኩት መልክ ለካርተር ደብዳቤ ተጽፎ እሳቸውም ሆነ እነመለስ ለዚህ የሚሰጡት መልስ ታይቶ ከዚያ በኋላ የምንነጋገርበት ነጥብ የሁን:: መልሳቸው ብዙ ቁም ነገር ይኖረዋል:: ወይ በግለሰብነቱ በፈጸመው ወንጀል ይዘነዋል ይበሉ፤ ወይ ደግሞ በቀንጅት መሪነቱ ነው ካሉ ለሌሎቹ መሪዎች ሴፍ ፖሲጅ እንሰጣለን እሱን ግን ይዘን እንቀጥላለን ብለው ይህንን ቀራኔ ለኛም፤ ለጂሚ ካርተርም ያብራሩ:: እንደሚገኘው መልክ ተወያይተን የሚቀጥለውን ርምጃ እንወስናለን::

ለ/ሌላው የአጀንዳ ነጥብ ፕሮፖዝድ መሆን ያለበት አመጽን በማውገዝ፤/ይህም ማለት ጠር ማንሳትና መዋጋት ብቻ ሳይሆን ማሰር፤ ማንገላታት፤ ከሥራ ማባረርን ይጨምራል/ ልዩነቶችን ያለአመጽ ለመፍታት የምንስማማበት አንድ የጋራ መግለጫ ማውጣት::

ጠ/ ተቃዋሚ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ህጋዊ ሰውነት አግኝተው ስለሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ተወያይቶ መወሰንና ይህንንም ወዲያው ተግባራዊ ማድረግ::

እነዚህን የአጀንዳ ነጥቦች ስናቀርብ ግልጽ ማድረግ ያለብን በዋና ዋና ጥያቄዎች /ሰብስታንሻል ኢሹስ/ ላይ መደረግ ያለበትንና የምንፈልገውን ድርድር ለማዘግየት ሳይሆን እንዲያውም ይህ ድርድር በጥሩ ሁኔታ የሚካሄድበትን አካባቢ ለመፍጠር እንደሆነ ሊገለጽላቸው ይቸላል::

ሌላው መነሳት ያለበት ነጥብ "አስበንበትና ተወያይተንበት እንዲሁም አግባብ ካላቸው የቀንጅቱ አካላት [illegible] ማንዴት ይዘን ለመምጣት እንድንችል ኢህአዴግ በበኩሉ በዚህ ስብሰባ ላይ ሊያነሳ የሚፈልጋቸውን የድርድር አጀንዳዎች በቀድሚያ እንዲገልጽልን" ብሎ መጠየቅ የግድ አስፈላጊ ነው:: እንዲሁ እንወያይ ተብሎ መሄድና በር ዘግቶ መወያየቱ ለኛ አጅግ በጣም አደገና ነው:: ህዝቡንም ሆነ አባሎቻችንንና ደጋፊዎቻችንን ወደጉን ትተን:: ስለዚህ ከሁሉም ወገን የሚቀርበው አጀንዳ ታውቆ ዝግጅት ተደርጎበት መሄድ ዋና ጉዳይ ይመስለናል:: ዋይም ደግሞ እኛ አጀንዳ የለንም እነሱ በሚያቀርቡት ነጥብ ላይ ለመወያየት ዝግጁ ነን ይሉ ይሆናል:: ይህ ከሆነ ደግሞ የሚቀጥለውን ርምጃ ከመልሳቸው በኋላ እንወስናለን:: ዋናው ነገር ግን የዚህ የአጀንዳ ነጥብ መቅረብ የግድ ይኖርበታል::

መድህኖቸና ምክር ቤቱ ጋር ባስቸኳይ ግንኙነት አድርጉ ለጊዜው እና በዚህ ውሱን አጀንዳ ለመንቀሳቀስ ብንችል መልካም ነው ብለን እንዳሰብን ተገልጾላቸው በዚህ ጥያቄ ላይ የጋራ አቋም ብንይዝ መልካም ይመስለናል::

ከእንግዲህ በኔ ግምት ዴሊኬት የሆነ ፌዝ ውስጥ እየገባን ስለሆነ ስለ ሂደቱና ስለና አቋም፤ ስለደብዳቤ ልውውጦች ወዘተ ለህዝቡ በሬዲዮቸን በየጊዜው መግለጫዎች መስጠት ይኖርብናል:: ካስፈለገ ለዚህ ጉዳይ አንድ ሰው ይመደብ::

ነገደ